ወገን ለወገኑ ይድረስ!

ኢብሳ ነመራ

ሰውና የተፈጥሮ አደጋ አብረው ነው የሚኖሩት። የአየር ንብረት መዛባት የሚያስከትለው ድርቅ፣ አውሎ ንፋስ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ . . . ጊዜና ቦታ ሳይመርጡ ሲከሰቱ ኖረዋል። እንደየክብደታቸው መጠን ህይወት አጥፍተው፣ ንብረት አውድመው፣ ሃገር አመሳቅለው አልፈዋል። የሰው ልጅ በእስካሁን ስልጣኔው የተፈጥሮ አደጋዎችን እንዳይከሰቱ ማስቀረት አልቻለም። በሰው ላይ የሚያደርሱትን አደጋ መቀነስና መከላከል ግን ችሏል። ሰው የተፈጥሮን አደጋ ባይፈጥርም፣ በራሱ እጅ የሚያባብስበት ሁኔታ ደግሞ አለ። በተለይ ከአየር መዛባት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ድርቅና ጎርፍ የመሳሰሉትን አደጋዎች፤ ይህን የሚያደርገው የተፈጥሮ አካባቢውን ያለአግባብ በመጠቀም፣ አየርን በመበከልና የከባቢ አየር ሙቀት እንዲጨምር በማድረግ፤ ወዘተ. ነው። ይህን አባባሽ ምክንያት ሰው ራሱ ሊያስተካከለው ይችላል።

በሰው ሰራሽ ምክንያት በአየር ንብረት ላይ የሚመጣው ለውጥና ለውጡ በሰው ልጅ ላይ የሚያስከትለው ቀጥተኛ ተጽእኖ አሳሳቢ የሆነበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። የአየር ንብረት ለውጥን በተለይ የከባቢ አየር ሙቀትን የመከላከል ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ የተጀመረው ለዚህ ነው። እስካሁን ግን ከተስፋ ያለፈ ምንም ተጨባጭ ለውጥ አልተገኘም ማለት ይቻላል። በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ በሚከሰት ድርቅ በተደጋጋሚ ስትመታ የኖረችውና ከቅርብ ገዜ ወዲህ ደግሞ ይህ ሁኔታ እየተባባሰባት የመጣችው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና እንዳላት ይታወቃል። የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ ቀርፆ እንቅስቃሴ በመጀመር ረገድም የመጀመሪያዋ አገር ነች። አሁንም ግን በድርቅ ከፉኛ እየተመታች ትገኛለች።

በ2007 ዓ/ም የበልግና ክረምት ዝናብ ስርጭት በመዛባቱና በአንዳንድ አካባቢዎች መጠኑ በእጅጉ በመቀነሱ የምስራቅ ኦሮሚያ፣ የምስራቃዊ አማራ አካባቢዎች፣ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የተለያዩ አካባቢዎች፣ የአፋርና የኢትዮጵያ ሶማሌ፣ የድሬዳዋ ዙሪያ አካባቢዎች በድርቅ ተፅእኖ ስር ወድቀዋል። ይህ በሃምሳ ዓመት ውስጥ በአስከፊነቱ ወደር ያልተገኘለት ድርቅ 10 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ለምግብ እጥረት አጋልጦ እንደነበረ የታወሳል። ይህን የድርቅ ተጽእኖ የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ፣ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ሳይፈናቀሉ፣ የህጻናትና የወጣቶች ትምህርት ሳይስተጓጎል መከላከል ተችሏል። የድርቁን ተጽእኖ በመከላከሉ ተግባር የኢፌዴሪ መንግስት የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። መንግስት ድርቁ ያስከተለውን የምግብ እጥረት ተጽእኖ ለመከላከል የ16 ቢሊዮን ብር በጀት መድቦ የተቀናጀ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የማቅረብ ስራ ማከናወኑ ይታወሳል። ይህ የቅርብ ትውስታችን ስለሆነ የድርቁን ተጽእኖ ለመከላከል የተከናወኑትን ተግባራት በዝርዝር ማንሳት አያስፈልግም። የድርቁን ተጽእኖ በመከላከል ረገድ ከዚያ ቀደም ከነበረው ሁሉ በተለየ መንግስት የአንበሳውን ድርሻ ሊይዝ የቻለው ባለፉት አስራ ሶስት ዓመታት በተመዘገበው ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት መሆኑ ግን ሊታወስ ይገባል። የድርቅን ተጽእኖ የመከላከል የውስጥ አቅም ተፈጥሯል ማለት ነው።

ያም ሆነ ይህ፤ ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ በሆነ የአየር መዛባት ምክንያት የሚከሰት ድርቅ የጉዳት ተጽእኖው የአምናውን ያህል ባይሆንም ዘንድሮም ኢትዮጵያን መትቷታል። የዘንድሮው ድርቅ የተከሰተው በኢትዮ ሶማሌ ክልል ዘጠኝ ዞኖች፤ በኦሮሚያ በቦረና፣ በባሌ ቆላማ ስፍራዎች፣ በጉጂና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፤ በደቡብ ክልልም በሰገን አካባቢ፣ ጋሞ ጎፋ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ድርቅ ተከስቷል። በዚህ ድርቅ ሳቢያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች ለአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ ጠባቂነት ተዳርገዋል። በድርቁ ሳቢያ የአርብቶ አደሩ ኑሮ የተመሰረተባቸው ከብቶች ለአደጋ ተጋልጠዋል።

ለእነዚህ በድርቅ ተጽእኖ ስር ለወደቁ ዜጎች የዕለት ደራሽ እርዳታን ጨምሮ ለሰብዓዊ ድጋፍ 948 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግም የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን አስታውቋል። ኮሚሽኑ እንዳስታወቀው ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ካለፈው የተሸጋገረ በጀት ታሳቢ ሲደረግ፣ 715 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያስፈልጋል። ከጠቅላላው ገንዘብ ውስጥ 598 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለምግብ አቅርቦት፣ 105 ሚሊዮን ዶላር ለተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት፣ 129 ሚሊዮን ዶላሩ ለጤና፣ ለትምህርትና ለእርሻ እንዲሁም ለተፈጥሮ ሃብት ድጋፍ፣ ቀሪው ገንዘብ ደግሞ ከንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እስከ ቁሳቁስ ድጋፍ ድረስ እንደሚውልም ኮሚሽኑ ይፋ አድርጓል።

ይህ ለእርዳታ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከመንግስት በተጨማሪ የሁለትዮሽ ስምምነት ባላቸው ተራድኦ ድርጅቶች እንደሚሟላ፤ ተራድኦ ድርጅቶችም ይህንን ተገንዝበው በተሰማሩበት የሰብዓዊ እርዳታ ስራ የበኩላቸውን እንዲወጡ ኮሚሽኑ ጥሪ አቅርቧል። መንግስት ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ከወዲሁ ከ47 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ ድጋፉን ማስቀጠሉንም ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በኢትዮጵያ የሚገኙ የዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅቶች ተወካዮችም ኢትዮጵያ የባለፈውን ዓመት ድርቅ የተቋቋመችበትና ድርቅ በተከሰተበት አካባቢ የሚገኙ ዜጎችን የታደገችበት መንገድ የሚደነቅ መሆኑን አስታውቀዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ ተራድኦ ድርጅት የኢትዮጵያ አስተባባሪ አሁና ኢዚአኮንዋ አገሪቷ በዚህ ደረጃ ድርቁን ተቋቁማ የመጣችበት አሰራር የተሻለ ልምድ በማካበት ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ ያስችላታል ብለዋል። አስተባባሪዋ የተራድኦ ድርጅቶች ተሳትፎ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፣ በአይነት ከሚቀርብ ድጋፍ ባሻገር ለንጹህ ውሀ አቅርቦት የሚደረገው ድጋፍ ከወዲሁ መጀመሩን ጠቁመዋል።

28ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ አስታከው በአዲስ አበባ ጉብኝት ያደረጉት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬስ እና የድርጅቱ የእርዳታ ዋና ኃላፊ ስቴፈን ኦብራይን የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያ መንግሥት በአገሪቱ የተከሰተውን ድርቅ ለመከላከል ለሚወስደው እርምጃ ድጋፍ እንዲሠጥ ጥሪ አድርገዋል። ጉቴሬዝ በየትኛውም የዓለም አካባቢ ለሚከሰት ድርቅ ምላሽ መሥጠት የበጎ ምግባር ሥራ ብቻ ሳይሆን ፍትሃዊነትና የዓለምን ጥቅም የማስከበር ጉዳይ ነው ብለዋል። የድርጅቱ እርዳታ ኃላፊ ስቴፈን አብራይን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እኤአ በ2017 ለሰብዓዊ እርዳታ ያስፈልገኛል ብሎ ላቀረበው ድጋፍ ዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ምላሽ እንዲሠጥ ጥሪ አቅርበዋል። በዚህ ጥሪ መሰረት ድጋፍ ሊገኝ ይችላል የሚል ተስፋ አለ።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በቅርቡ በኦሮሚያ ቦረና ዞንና በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ደቡብ ኦሞ ዞኖች በድርቅ የተጠቁ የአርብቶ አደር መኖሪያ አካባቢዎችን ጎብኘተው ነበር። በሁለቱም ክለሎች የሚኖሩ የድርቅ ተጠቂ አርብቶ አደሮች ከብቶቻቸው እያለቁ መሆኑን ለምክር ቤቱ አባላትና አብሯቸው ለተጓዘው የመገናኛ ብዙሃን ቡድን ገልጸዋል። አንድ የቦረና አርብቶ አደር ስለሁኔታው ሲያስረዳ 250 ከብቶች እንደነበሩትና ከእነዚህ ውስጥ 200 ያህሉ መሞታቸውን አስታውቋል። በአየር መዛባት ምክንያት የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም መንግስት ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ያልካዱት አርብቶ አደሮቹ ፣ ድጋፉ ግን በቂ አይደለም ብለዋል። በተለይ የእንስሳ መኖ አቅርቦቱ ካላቸው እንስሳ ቁጥር ጋር ሲነጻጻር እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው የገለጹት፤ እንደ አርብቶ አደሮቹ ገለጻ፤ በመንግስት የሚቀርብላቸው የመኖ ድጋፍ ከአምስት እንስሳ በላይ መመገብ አይችልም። የእንሰሳቱ ማለቅ ምክንያትም ይህ እንደሆነ ነው የሚናገሩት፤ ከብቶቻቸው እጅግ በጣም ስለከሱ ለገበያ ቢያቀርቧቸውም ጥሩ ዋጋ ማውጣት እንዳልቻሉ ተናግረዋል።

እርግጥ በተደጋጋሚ ሲገለጽ እንደቆየው የኢፌዴሪ መንግስት በድርቅ ለተጠቁት የአርብቶ አደር አካባቢዎች እርዳታ ማቅረብ የሚያስችል በቂ አቅም አለው። በድርቁ ሳቢያ የአንድም ሰው ህይወት እንደማይጠፋ በእርግጠኝነት ተናግሯል። በዚህ መሰረት እርዳታ ማቅረብ ጀምሯል። ይሁን እንጂ፤ በአርብቶ አደሩ እጅ ላሉት ሁሉም ከብቶች መኖ የማቅረቡ ጉዳይ የሚቻል አይደለም። ስለዚህ የገበያ ትስስር በመፍጠር አርብቶ አደሩ ጥቂት የዘር ከበቶችን አስቀርቶ ሌሎቹን እንዲሸጥና ገንዘቡን እንዲይዝ ለማድረግ እየተሰራ ነው። ዝናብ እስኪጥል ድረስ በድርቅ ወዳልተመቱ አካባቢዎች እንዲሄዱም እየተደረገ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብና ተቋማት፣ እንዲሁም የክልል መንግስታት ከኢፌዴሪ መንግስት ጎን ሆነው የድርቁን ተጽእኖ ለመከላከል ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እስካሁን ግን ድርቁ የተከሰተባቸው የክልል መንግስታት ብቻ ናቸው እርዳታ በማቅረብ ላይ የሚገኙት። ከድርቁ ተጽእኖ ነጻ የሆኑ ክልላዊ መንግስታትም እጃቸውን ሊዘረጉ ይገባል። ይህ የወገን ለወገን ድጋፍ ባለፈው ዓመት የተከሰተውን የድርቅ ተጽእኖ ለመከላከል በተደረገው ርብርብ ላይ በተግባር ታይቷል።

ለማስታወስ ያህል የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 684 ሚሊዮን ብር የእርዳታ በጀት መድቦ ነበር። ለመጠባበቂያ ፈንድ ድጋፍ ከህብረተሰቡ 34 ነጥበ 1 ሚሊዮን ብር፤ እንዲሁም ከክልሉ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሰራተኞች ከደሞዛቸው በማዋጣት የ96 ሺህ ብር ድጋፍ ቀርቧል። የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 200 ሚሊዮን ብር ነበር የመደበው። የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) 30 ሚሊዮን ብር እርዳታ ሰጥቷል። የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 130 ሚሊዮን ብር በጀት የመደበ ሲሆን፣ ከህብረተሰብ ለህብረተሰብ እርዳታ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አሰባስቦ ነበር። የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት 78 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር መድቦ ነበር። ከህዝብ ድጋፍ 17 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር አሰባስቦ ነበር። የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 52 ሚሊዮን ብር በጀት መድቧል። የክልሉ ነጋዴዎች 20 ሚሊዮን፣ የክለሉ የመንግስት ሰራተኞች ከደሞዛቸው 11 ሚሊዮን፣ የክልሉ ልዩ የፖሊስ ሃይል 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር፤ እንዲሁም ከህብረተሰቡ የተወጣጡ 30 ሺህ ከብቶች ለድጋፍ ተሰብስበዋል። የትግራይ ክልላዊ መንግስት 26 ሚሊዮን ብር በጀት ሲመድብ ባለሃብቶች የውሃና የእንስሳት መኖ ድጋፍ አድርገዋል። የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በዙሪያው ለሚገኙ በድርቅ ለተጠቁ የገጠር ቀበሌዎች የሚውል 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን፣ የሃራሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር በጀት መድበው ነበር። በተለይ የህብረተሰቡ የእርዳታ ተሳትፎ ዘንድሮም ሊቀጥል ይገባል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ ከፌዴራል መንግስት ጎን ለጎን በድርቁ የተጠቁ ክልሎች መንግስታት እርዳታ በማቅረብ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች በ60 ሚሊዮን ብር ድጋፍ እያደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግስትም 300 ሚሊዮን ብር መድቦ ለድርቁ ተጽእኖ ምላሽ እየሰጠ ይገኛል። የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እንስሳቱን ከፓርኮች መኖ ሰብስቦ በማምጣት ከፌዴራል መንግስት ከተሰጠው መኖ ጋር ቀላቅሎ ለእንስሳቱ እያቀረበ ይገኛል።

በአጠቃላይ ዘንድሮ በተለይ በአገሪቱ ቆላማ የአርብቶ አደር መኖሪያ አካባቢዎች የተከሰተውን ድርቅ ተጽእኖ በመከላከል ተግባር ላይ የኢፌዴሪ መንግስት ከክልል መንግስታት ጋር በመቀናጀት የአንበሳውን ድርሻ ይዘው እየተንቀሳቀሱ ነው። ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችም በተወሰነ ደረጃ ድጋፍ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። የኢትዮጵያ ህዝብና ተቋማትም እርዳታና ድጋፍ በማድረግ ረገድ የሞራል ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑ መታሰብ አለበት። “ስለምን?” ቢሉ፤ ወገን ለወገኑ መድረስ ይጠበቅበታልና!